# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE ONE: “የህይወቴ ምርጡ ቀን”

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1 : ምህረት AT HOME WITH HER PARENTS**

- ምህረት (F, 15)
- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)

**SCENE 2 : ንጉሴ AND HIS MOTHER AT THE SHOPPING MALL**

- ወይዘሮ ዘውዲቱ (F, 35)
- ንጉሴ (M, 16)

**SCENE 3 : ዳንኤል KANYAMA ARRIVES AT BONGO ACADEMY**

- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- ዳንኤል (M, 15)

**SCENE 4 : NIGHT-TIME AT ምህረት'S HOME IN THE SLUMS**

- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)
- ምህረት (F, 15)

**INTRO / NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ድራማ ተከታታዮች፣ በዚህ አዝናኝ እና አስተማሪ በሆነዉ ዝግጅታችን መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ የተሰኘ አዲስ እና ተከታታይ የራድዮ ድራማ ይዘን ቀርበናል። ዛሬ በምናደምጠዉ የመጀመሪያ ክፍል ጭዉዉት፥ ከባድ አማራጮችን እየተጋፈጡ ያሉ ሶስት አዳጊ ተማሪዎችን እንተዋወቃለን።

ከእነዚህ መካከል አንዷ ድሀ ቤተሰብ ያላትና፤ ወደፊት የተሸለ ህይወት እንዲኖራት በመታገል ላይ ያለችው ዉባና ብልኋ የ15 አመት ወጣቷ ምህረት ሙላቱ  ናት፡፡ ሌላዉ ፤ የተደላደለ ቤተሰብ ልጅ ምሳሌ የሚባልና ታዋቂ ለመሆን የሚታገለዉ የ16 አመቱ ንጉሴ ጃለታም አለ፡፡ በመጨረሻ ቤተሰቦቹ በጎረቤት ሀገር ላቦሪያ የሚኖሩትና የተሻለ የሚሉትን ትምህርት እንዲማርላቸዉ ወደ ውጪ የላኩት ዳንኤል ካሳሁንን እናገኛለን፡፡ ዳንኤል ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ስኬታማ በሆነዉ በአባቱ የወርቅ ማዕድን ድርጅት ስራ ይጠብቀዋል፡፡

እነዚህ አዳጊ ልጆች በአስቸጋሪ፣ በፈጣን ለውጥ ላይ ባለ ዓለም የተከበቡ ሲሆን በየእለቱ የትኛውን የህይወት መንገድ መምረጥ እንዳለባቸው ግራ በሚያጋባ መንታ መንገድ ላይ ቆመው እራሳቸውን ያገኛሉ፡፡ ዛሪሬ የምንጀምረዉ የህይወቴ ምርጥ ቀን በሚል ርዕስ በተዘጋጀዉ የመጀመሪያ ክፍል ድራማ ነዉ። ምህረት በቀድሞ ትምህርት ቤቷ እየጠበቃት የነበረዉን ደብዳቤ ወስዳ  ካነበበች በኋላ ያየችዉን መልክት  ፈጽሞ ማመን አቅቷታል፡፡

**SCENE 1: ምህረት AT HOME WITH PARENTS**

2. **SFX: SLUM DWELLING ATMO**

3. **SFX: FOOTSTEPS. ምህረት RUNS IN.**

4. **ምህረት፡** (screaming through door) እማ፣ ይህን የምታምኝ አይመስለኝም!

5. **SFX: CASSAVA BEING PEELED**

6. **ወ/ሮ ሉሊት፡** (frightened) ምህረት፣ እንደዚህ አታስደንግጪኝ! ስለ እግዚአብሔር ብለሽ፤ ነፍሰ ጡር እኮ ነኝ፤ ድንጋጤው ምጥ እንዲለቅብኝ አልፈልግም።

7. **ምህረት፡** እማ፣ ዛሬ በህይወቴ ምርጥ የምለው ቀን ነው!

***KW BEGIN***

8. **ወ/ሮ ሉሊት፡** (ironically) ተይ እንጂ፤ እውነትሽን ነው? ስለእዚህ አሁን እራት ሳዘጋጅ ልታግዢኝ ነው ማለት ነዉ ? ፈጽሞ እንዲህ በጉጉት ተውጠሽ አይቼሽ አላዉቅም...

9. **ምህረት፡** እንዴ፣ እማ፣ እባክሽን! ስሚኝ! ነገሩ እኮ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው።

10. **ወ/ሮ ሉሊት፡** (calmly) እሺ፣ እሺ፤ ልጄ፥ እሰማሻለሁ። ምንድን ነው ነገሩ?

11. **SFX: ሠ/ሮ ኵኪቱ STOPS PEELING CASSAVA**

***KW END***

12. ምህረት፡ (happily) ከትምህርት ቤታችን ፕሬዚዳንታዊ የገንዘብ ድጋፉን ለማግኘት ብቸኛዋ ዕጩ ተማሪ ሆኜልሻለሁ! ይህ የገንዘብ ድጋፍ የሁለተኛ ደረጃ አጠቃላይ የትምህርት ክፍያ ወጪዬን ይሸፍናል!ከቦንጎ አካዳሚ የተላከልኝ ይህ ደብዳቤ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው። ደብዳቤውን ያመጣሁት ከቀድሞው ትምህርት ቤቴ ነው። እዚያ ያሉ መምህራን በሙሉ በእኔ በጣም ነው ደስ ያላቸው, , ,እናልሽ, , ,

13. ወ/ሮ ሉሊት፡(sighs) ምህረቴ፣ የምወድሽ ልጄ ጎበዝ እንደሆንሽ አውቃለሁ በዚያ ላይ ትምህርትሽን መቀጠል እንደምትፈልጊ ይገባኛል። ግን ...ይሄን አሁን እንዴት ብዬ እንደምነግርሽ እንጃ... እኔስ ሌላ በሆነ ነበር ምኞቴ...

14. ምህረት፡ እማዬ ይሄ እኮ የተለየ ነው ። ተመልከች ከአንቺ እና ከአባዬ የምፈልገው ትምህርቱን ለመጀመር የሚያስፈልጉኝ ጥቂት ነገሮችን እንድትገዙልኝ ብቻ ነው። ቀሪው ሁሉ ማለትም የትምህርት ቤት ክፍያዎች እና ሁሉም ነገር በሚሰጠኝ ፕሬዚዳንታዊው የገንዘብ ድጋፍ የሚሸፈን ነው! ቦንጎ ትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ ቤተ-መጽሐፍት አላቸው፣ የኮምፒዩተር ክፍል ...

15. **SFX: IRON SHEET DOOR BEING PUSHED OPEN**

16. **SFX: FOOTSTEPS - አቶ ሙላቱ COMES IN**

17. ምህረት፡ (enthusiastic) እንዴ፣ አባዬ! ያገኘሁትን ነገር መቼም ገምተኸው፤ አስበኸዉ አታውቅም!! (hugs her father)

18. SFX CLOTH RUSTLING

19. ምህረት፡ (while hugging her father) ቦንጎ አካዳሚ ተቀብሎኛል!

20. አቶ ሙላቱ፡ (reserved) እረእረረረ! ምንድን ነው ይሄ? ደግሞ እንዲህ አትቀፊኝ ወገቤን ሰበርሽው እኮ!

21. ምህረት፡ ተመልከት! ይህ-ትምህርት ለመጀመር የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ዝርዝር ነው።

22. አቶ ሙላቱ፡ (drunk tone) ምን,,,,,? ለ12 ሰዓታት ፀሃይ ላይ ተገትሬ እንዲያ የማንንም ቤት ስጠብቅ ቆይቼ ስመጣ የምትቀበይኝ በዚህ መልኩ ነው ማለት ነዉ?

23. ወ/ሮ ሉሊት፡ ሙላቱ ፣ ልጅህ በደስታ ሰማይ ልትነካ ነዉ! ፕሬዝዳንቱ የሆነ ገንዘብ ሰጥቶኛል እያለች ናት!

24. አቶ ሙላቱ፡፡ (curious) በእውነት? አሁን አመጣሽው፤ እንዲህ አይነቱ አቀባበል እማ ደስ ነው የሚለኝ። እስኪ አሳዩኝ እስኪ ልየዉ.

25. SFX: PAPER SNATCHED RAPIDLY FROM HAND

26. **አቶ ሙላቱ፡፡** (reads out aloud sarcastically እህ! “ውድ ምህረት ሙላቱ እንኳን ደስ አለሽ! በአንደኛ ደረጃ ትምህርትሽ ባመጣሽው ድንቅ የፈተና ዉጤት ለሌሎቹ ተማሪዎች አብነት ሆነሽ በመገኘትሽ በቦንጎ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተሽ እንድትማሪ ተፈቅዶልሻል፡፡ በተጨማሪም ከፕሬዝዳንታዊው የገንዘብ ድጋፍ ተጠቃሚ ጥቂት ተማሪዎች መካከል ም አንዷ ሆነሽ ተመርጠሻል፡፡ ይህ የገንዘብ ድጋፍ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትሽን ጠቅላላ የመማሪያ ክፍያዎች ይሸፍናል፡፡ በሀገሪቷ አለ በሚባለው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚቀጥለውን መንፈቀ ዓመት ከመጀመርሽ በፊት የሚከተሉትን እቃዎች መግዛት ይኖርብሻል፡፡ 1. ሁለት የትምህርት ቤት የደንብ አልባሳት፣ 2. ሁለት ጥንድ ጥቁር ጫማዎች (ቦንጎ የሚመክረው ቆዳ ጫማ ቢሆን ነው)፣ 3. አንድ ጥንድ የስፖርት ጫማ፣ 4. አንድ ሙሉ የጂኦሜትሪ መማሪያ መሳርያ … አርቲ፣ ቡርቲ፣ ቡቱቲ ምናም፣ እንዴ! ቆይ ግን እነዚህ ሰዎች ማን መስለናቸዋል? ለእራሴ እራቴን ድንች ቀቅዬ ነው የምበላው እነሱ ጭራሽ ለሴት ልጄ ሁለት ጥንድ ቆዳ ጫማዎች መግዛት ይችላል ብለው ይጠብቃሉ? ሁለት ጥንድ ቆዳ-

27. **ምህረት፡** (scared) ግን እኮ አባዬ፣ መሞከር የምንችለው እ –

28. ወ/ሮ ሉሊት፡ ምህረት ፣ ስለ እዛ ምንም ጥርጥር የለውም፣ እራስሽን ኩሩ አድርገሻል። ይልቅ አሁን ነይና ድንቹን በመላጥ አግዢኝ።.

29. ምህረት፡ እማዬ! ከአክስቴ ለምለም ገንዘብ መበደር እንችላለን፣ አንችልም? አቅም ያላት ይመስለኛል! ማለቴ ሁለቱን ትናንሽ ወንድሞቼን ወስዳ እየተንከባከበቻቸው፣ እያሳደገቻቸዉ ነው እና …እርሷ… እርግጠኛ ነኝ,,,እ

30. አቶ ሙላቱ፡፡ (very angry) አፍሽን ዝጊ ምህረት! ዝጊ! የምልሽን ስሚ! ስለ አክስትሽ እና ሁለቱ ወንድሞችሽ ለማንም ስትናገሪ መስማት አልፈልግም። ግልጽ ነው? ገባሽ አይደል?

31. ምህረት፡ ግን …አባዬ አልገባኝም። ስለዚህ ጉዳይ መነጋገሩ ምን ጥፋት አለው?

32. አቶ ሙላቱ፡፡ (firmly) አሁን ከአንቺ ሌላ መልስ አልፈልግም! ሂጂና እናትሽን ድንቹን በመላጥ አግዣት። ያው ሄድኩላችሁ።

**33. SFX STEPS አቶ ሙላቱ LEAVES**

34. ወ/ሮ ሉሊት፡ (pleads) ሙላቱ እባክህ አታምሽ ምግቡ ይቀዘቅዛል። እና ደግሞ ይኸውልህ፤ በጣምም አትጠጣ እባክህ!

**35. SFX: IRON SHEET DOOR CLOSES**

**36. MUSIC TRANSITION**

**<u>SCENE 2: ንጉሴ AND HIS MOTHER AT THE SHOPPING MALL</u>**

37. SFX: CAR STOPS AND PARKS. INSIDE THE CAR:

38. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡ ፡ መልካም፣ ንጉሴ እዚህ እጠብቅሀለሁ.

39. ንጉሴ፡ የምር እማዬ ምንም ችግር የለዉም፡፡ በመኪና ማቆሚያ ስፍራ እኔን ቁጭ ብለሽ መጠበቅ የለብሽም.

40. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡ ፡ ንጉሴ ፣ ወደዚያ የገበያ ስፍራ ብዙ ገንዘብ ይዘህ እየሄድክ ነው፡፡ በመጀመርያ በሰላም መግባትህን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ እሄዳለሁ፡፡

41. ንጉሴ፡ አሁን እኮ አስራ ስድስት አመት ሞልቶኛል እማ፡፡ እራሴን መጠበቅ እችላለሁ፡፡.

42. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡ እውነት ነው፣ ንጉሴ ጃለታ ትልቅ ሰው እየሆነ ነው! አውቃለሁ፡፡ እና እንደ ህጻን ልጅ ልቆጣጠርህ አልፈልግም፡፡ ገንዘብ የምሰጥህም ለትምህርት ቤት የሚያስፈልግህን እራስህ መግዛት እንድትችል ነዉ። (proudly) የኔ ልጅ በቦንጎ አካዳሚ! እምም፣ ጓደኞቼን አግኝቼ ስለ አንተ እያነሳሁ በጉራ ላቅራራባቸው ቸኩዬአለሁ።

43. ንጉሴ፡ (annoyed) እማ …የሚገዙትን እቃዎች ዝርዝር ማየት እችላለሁ?

44. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡ በታብሌት ኮምፕዩተሬ ላይ ነው የጻፍኩት፡፡

**ታብሌቱን ይዘኸው ልትሄድ ትችላለህ፡፡ የቦንጎ አካዳሚ ተማሪ ከምን አይነት ቤተሰብ እንደመጣ ለሰዎች ማሳየት ያስፈልገዋል፡፡ እንዳይጠፋብህ ብቻ እርግጠኛ ሁን፡፡ እናም የምትገዛውን ነገር ሁሉ ገዝተህ እንደጨረስክ ደውልልኝ እና መጥቼ እወስድሀለሁ፡፡ ረጋ ብለህ እየተዝናናህ ግዛ!**

**45. SFX: TABLET HANDED OVER**

**46. ንጉሴ፡** **አመሰግናለሁ እማዬ፡፡ እንግድያዉ እስከ በኋላ!**

**47. SFX: CAR DOOR OPENS, ንጉሴ DESCENDS, DOOR CLOSES.**

***KW BEGIN***

**48. ATMO: URBAN ATMO, SHOPPING MALL ATMO IN THE DISTANCE**

**49. SFX: ELECTRIC CAR WINDOW WOUND DOWN (from outside)**

**50. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡** **እንዴ ንጉሴ! ሌላ አንድ ተጨማሪ ነገር.**

**51. ንጉሴ፡** (bored) **ምንድን ነዉ አሁን እማዬ?**

**52. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡** (whispers) **ስለ ገንዘቡ ለአባትህ ለጃለታ እንዳትነገረው እሺ፡፡ እሱም በበኩሉ የሆኑ ነገሮች ሊገዛልህ ሱቅ ይዞህ ሊሄድ እንዳሰበ አውቃለሁ፡፡ ስለእዚህ ብልጥ ሆነህ ዛሬ የገዛኸዉን ነገር ከደበቅህ፤ ትምህርት ቤት ስትጀምር ከምትፈልገው በላይ አስፈላጊ እቃዎች ይኖሩሀል፡፡**

**53. ንጉሴ፡** **እስከ በኋላ እማ!**

54. ወይዘሮ ዘውዲቱ፡ ንጉሴ- እንደዉ ግን ታዉቃለህ አይደለም በአንተ በጣም፣ በጣም እንደምንኮራብህ!

55. SFX: ELECTRIC CAR WINDOW UP (from outside)

56. SFX: CAR DRIVES OFF

*KW END*

57. MUSIC TRANSITION

**SCENE 3: ዳንኤል KANYAMA ARRIVES AT BONGO ACADEMY AND MEETS PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ**

58. SFX: SCHOOL OFFICE ATMO

59. ርዕሰ መምህርት ሰብለ፡ እሺ,,, ስሜ ዳንኤል ካሳሁን ነው አልከኝ.

60. ዳንኤል: አዎ ልክ ኖት፣ እትዬ.

61. ርዕሰ መምህርት ሰብለ፡ እና የእዚህ ሀገር ነዋሪ አይደለህም፣ ልክ ነኝ?

62. ዳንኤል፡ ትክክል! ከላቦሪያ ነዉ የመጣሁት፤ የጉዞ ሰነዴን ይዣለሁ- ይኸው

63. ርዕሰ መምህርት ሰብለ፡ (cold) አሀ፤ መልካም፤ እና የትምህርት ቤት ክፍያውንም ይዘሀል? ከእኛ የመገበያያ ገንዘብ-ሌላ ገንዘብ አንቀበልም፣ የምንቀበለው,,,,

64. ዳንኤል፡ (interrupts her) ክፍያውን በዩኤስ ዶላር ይዣለሁ መምህርት።

65. ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ማለት የፈለግኩትም እሱን ነዉ። የምንቀበለው

ወይ የሀገር ውስጥ ገንዘብ አለበለዚያ የዩኤስ ዶላር ነው።
ታቀብለኝ?

66. **SFX: BANK NOTES HANDED OVER AND COUNTED BY HAND**

67. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** መልካም። ሁሉም ነገር ትክክል ይመስላል። ወደ ቦንጎ አካዳሚ እንኳን ደህና መጣህ፣ ዳንኤል! በዚህ የትምህርት ዘመን ከሚመዘገቡ የመጀመሪያ ተማሪዎች አንዱ አንተ ነህ። በዚሁ ትምህርት ቤት ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኘዉን የወንዶች ማደርያ ክፍልህን አሳይሀለሁ፤

68. **ዳንኤል:** እሺ,,, አመሰግናለሁ፣ አትዩ

69. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 4: NIGHT-TIME AT ምህረት'S HOME IN THE SLUMS**

70. **SFX: NIGHT ATMO IN SLUM SETTLEMENT**

**(speaking in hushed tones)**

71. **ወ/ሮ ሉሊት:** (in the distance: desperate) አይሆንም፣ ሙላቱ! ያንን ምህረት ላይ ማድረግ አንችልም። አይገባትም!

72. **አቶ ሙላቱ** (in the distance: loud) እና ከዚህ ሌላ የሚገባት ምንድን ነው ታድያ? እህ? አሁን ምህረት የ15 ዓመት ልጅ ናት። የሆነ ሰው ሚስት ለመሆንም ደርሳለች። ከዚህ በተጨማሪ ስለምናገኘው ጥሎሽ ሁሉ አስቢ እስኪ!

73. **SFX: ምህረት TURNING OVER IN BED**

74. **ምህረት:** ወይኔ፣ ይህማ አይሆንም! የምሰማው ነገር ልክ ነው ግን?

75. ወ/ሮ ሉሊት፡ ሙላቱ ድምጽህን ቀንስ! ምህረት እየሰማች ሊሆን ይችላል። በእኛ እና በእርሷ አልጋ መካከል የሚለየን የተጋረደው ብርድ ልብስ ብቻ ነው!

76. አቶ ሙላቱ፡ ሉሊት፣ ወስኛለሁ! ይህም የመጨረሻ ውሳኔዬ ነው። እባክሽን ያንን የናፍጣ ኩራዝ አጥፊና፤ ልተኛበት።

77. ወ/ሮ ሉሊት፡ (pleads) ሙላቱ፤ እባክህን የምትናገረውን ነገር በቅድምያ አስብና ተናገር። ወንዶች ልጆቻችን እህትህ ጋር ሄደው እንዲኖሩ ያስገደድከኝን ነገር መቀበሌን አሁንም ድረስ ለመቋቋም አልቻልኩም። እና አሁን ደግሞ...

78. አቶ ሙላቱ፡፡ ኩራዙን ማጥፋት ካልፈለግሽ እራሴው አጠፋዋለሁ።

79. SFX: BLOWING OUT OIL LAMP/ CANDLE

Silence

80. ምህረት፡ (suppressed crying) ይህ ሊሆን አይችልም!

81. MUSIC TRANSITION

**82. OUTRO/NARRATOR:**

ምህረት ከአባቷ ልብ የሚሰብር ዜና ሲወጣ ሰምታለች፡፡ በአሁኑ ወቅት መምረጥ ባለባት መንታ መንገድ ላይ ትገኛለች፡፡ እናስ ምን ለማድረግ ትወስን ይሆን? በዚህ መሀከል ንጉሴ እና ዳንኤል ለመጀመሪያ የትምህርት ቤት ቀናቸዉ እየተዘጋጁ ናቸው፡፡ የዳንኤል ቤተሰቦች ልጃቸዉን ለምን ወደ ቦንጎ አካዳሚ  ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደሚልኩት ማወቅ ትፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ በምስል የተቀረፀዉን አጠር ያለ ዘገባውን ከድረ-ገፅ አድራሻ dw.de/lbe ላይ ታገኙታላችሁ። በፌስ ቡክ አድራሻችንም ተከታተሉን። መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ የተሰኘዉን ተከታይ ክፍል ጭዉዉት ይዘን እስክንቀርብ እዚህ ላይ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።